# ይድረስ ለኤርምያስ ለገሰ: እነ ዶ/ር አብይ ማጽዳት የጀመሩት እናንተ ያቆሸሻችሁትን ነው (ይገረም አለሙ)

“ *ሥጋህን በኃጢአት እንዳያስተው አፍህ አርነት አትስጥ*” (*መጽሀፈ መክብብ* 5.6)

“ከቃልህ የተነሳ ትጸድቃለህ ከቃልህ የተነሳም ትኮነናለህ” (*ማቲዎስ* 12.37)



ኤርምያስ ለገሰ

*የዚህ ጽሁፍ መነሻ ዓላማም ሆነ መድረሻ ግቡ አቶ ኤርምያስ ለገሰ ለብዙዎቻችን የታየንና ተስፋ የሰነቅንበት በሀገራችን የሚታየው የለውጥ ጅማሮ አልታይ ብሎት ወይም ሆን ብሎ ማየት ባለመፈለግ የሚያሳየውና የሚያሰማው ነገር ነው፡*

*አቶ ኤርምያስ እኛም እንደምናውቀው እሱም በድፍረትና በኩራት እንደሚናገረው ማስታወቂያ ምኒስትርን የተካውና የአማርኛ ቃል ታጥቶለት የኮሙኒኬሽን ሚኒስቴር እየተባለ የሚጠራው መስሪያ ቤት ምኒስትር ዲኤታ (ሁለተኛ ሰው) ነበር፡፡ ያውም በበረከት ስምዖን ዘመን፡፡*

*እኛ በበረሀ ስንታገል እናንተ ከተማ ተቀምጣችሁ ጮማ በውስኪ ስታወራርዱ ኖራችሁ ዛሬ በስመ ዴሞክራሲ ሥልጣን መንጠቅ ያምራችኋል እንደ እኛ ጫካ ግቡና ሞክሩ በሚል አቋማቸው በምናውቃቸው ወያኔዎች ዘንድ ከበረሀ ታግሎ ላልመጣ ከከተማ ለተቀላቀለ የአራዳ ልጅ ለዚህ ደረጃ መድረስ እጅግ ከባድ ለመሆኑ አነጋጋሪ አይደለም፡፡*

*ስለሆነም ከጳጳሱ ቄሱ ይሉ አይነት ሆኖ መኖርን፣ አቤት ወዴት ብሎ መታዘዝን ሰጥ ለጥ ብሎ መገዛትን ወዘተ ይጠይቃል፡፡ አቶ ኤርምያስ ለዛ ሥልጣን የበቃው በዚሁ ሁኔታና መንገደ ብዙ ቦታዎችን ረግጦ የመሰላሉን ደረጃ ወጥቶ መሆኑ አያጠያይቅም፡፡ በዚህ ሁኔታ ከካዴሬነት እስከ ምክትል ሚኒስትርነት ሲደርስ ኢትዮጵያዊነትን እየዘመረ፤ ስለ አንድነት እየደሰኮረ፤ የኢትዮጵያን ታሪክ እያከበረና እየሰከረ ወዘተ ነበር ተብሎ አይታሰብም፤ እሱም አይልም፡፡ እርሱ ብቻ አይደለም እሱ ያሰለጠነ ያሰማራቸው ሁሉ ኢትዮጵያዊነትን ሲያራክሱ፣ አንድነታችንን ሲያንድፉ፣ልዩነትን ሲሰብኩና ጥላቻን ሲነዙ ነው የኖሩት፡፡*

ዶ/ር አብይን ሥልጣን በተረከቡ ወር ባልሞላ ግዜ ውስጥ የምሰማው ሁሉ ሥልጣንን ሳይሆን ሽሽትን የሚያሰመኝ ነው ብለው እስከመናገር ያደረሳቸው የሀገርና የህዝብ ችግር በደደቢቶች ተዘርቶ እነ ኤርምያስ በመኰትኰቶና ውሀ ማጠጣት ያሰደጉትና ያስፋፉት ነው፡፡ሀያ ሰባት አመት በሀገራችን ለተፈጸመው ጥፋት ሁሉ ዋና ተጠያቂ የሆነው መለስ እንደ ኤርምያስ አይነቶቹን አፈ ጮሌ የአራዳ ጩልሌዎችን ማሰለፍ ባይችል ያን ሁሉ ነገር ማድረግ ይችል ነበርን ብሎ መጠየቅ የእነ ኤርምያስን ድርሻና የጥፋት ደረጃ ብዛትና ክብደት ለመረዳት ያስችላል፡፡

ወደ ኋላ ተመልሼ ኤርምያስን የመውቀስ ፍላጎት የለኝም፣ ርጥቡ ሬሳ ደርቅ ያስነሳ ሆኖብኝ ነካካሁት እንጂ፡፡ ኤርምያስ ዶ/ር አብይ ወደ ሥልጣን ከመጡ ግዜ አንስቶ የሚናገረውና የሚጽፈው የትናንት እሱነቱን ያገናዘበ ሆኖ አልታይህ ቢለኝ ተረስቶ ከሆነ በሚል ለማስታወስም ነው፡፡

ኤርምያስ ህዝባዊው ተቃውሞ ምን ሽቶ እንዳጣ፣ ምን ተስፋ አድርጎ እንደ ጉም እንደበነነበት፣ በእነ ዶ/ር አብይ ወደ ሥልጣን መምጣት ምን ጠብቆ እንደረበት ግልጽ አላደረገም፤ ሊገልጸውም የሚችለው አይመስለኝም፡፡ ይህ ብቻም አይደለም መሰረታዊ የሚለው ለውጥ መቼ በማንና እንዴት? ሊመጣ እንደሚችል አልገለጸም፡፡ አብይን ባለመደገፍ ይልቁንም እሱ እንደሚለው ህዝባዊ ተቃውሞውን በማስቀጠልና የአብይን የሥልጣን ቆይታ በማሳጠር ምን ማትረፍ እንደሚቻል አላሳየም፡፡ ጅማሮውን ለውጥ ተስፋ ላደረግነው ሰዎች አልታይ ያለን ኤርሚያስ የሚያውቀው ወይንም አካ የሆነበት እቅድ ዝግጅት ይኖር ይሆን!

እነ አቶ ለማ ውስጥ ውስጡን ሲሰሩ፣ ሲዘጋጁና ሲያደራጁ ቆይተው ህዝባዊው ተቃውሞ ወደ መድረክ ለመወጣት ምቹ ሁኔታ ፈጥሮላቸው በወያኔ ሊበሉም ሆነ ሊቆሙ የማይስችል ደረጃ መድረሳቸውን ባረጋገጡበት ሰአት ወደ ባህር ዳር ተጉዘው በዘመነ መለስ በአማራና በኦሮሞ መካከል የተገነባውን የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ግንብ ሲያፈርሱ ጌታቸው ጋረደው ስሜቱን መቆጣጠር ተስኖት እሳትና ጭድ በማለት የተናገረው የእነ ኤርምያስን ሥራ ነው፡፡

በመሆኑም ኤርምያስ ከወያኔ ተፋታሁ ካለ በኋላ እንደመነግረን ከልቡ ለኢትዮጵያ ዴሞክረሲያዊ ሥርዓትን የሚመኝ ከሆነ፣ ወደዚህኛው ጎራ የተቀላቀለው የምር ተጸጽቶና ንስሀ ገብቶ እና ከልቡ አምኖ ከሆነ ዛሬ እነ አብይ ለጀመሩት የጽዳት ዘመቻ ግንባር ቀዳም ተሳታፊ እንጂ ነቃፊ ባልሆነ ነበር፡፡ ኢትዮጵያዊነትን ወደ መቀመቅ ለማውረድ፣ አንድነትን እሳትና ጭድ ለማድረግ፣ ታሪክን ለማዛባትና ህዝብን ረግጦ ለመግዛት የተፈጸሙትን ድርጊቶች ምንነት ብሎም ለምን እንዴት በማንና በምን ወዘተ አንደተፈጸሙ የሚያውቁ እንደ ኤርምያስ አይነት ሰዎች የበሽታ መድህኒት የሚገኘው ከዛው ከበሽታው በመሆኑ ሀገርን ለማዳን ለተጀመረው ህክምና ግንባር ቀደም ተሰላፊ ሊሆኑ ሲገባ እነርሱ ያቆሸሹት እንደ ቆሸሸ እንዲቀጥል እነርሱ ለበሽታ የዳረጉት ከህመሙ እንዳይፈወስ የሚፈልጉ የሚያመስላቸው ድርጊት ሲታይባቸው ምነዋ! የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ጩኸት ውሸትና ሽፋን ነው እንዴ! የሚል ጥርጣሬ ያጭራል፡፡

ስለሆነም ከተራ ካድሬነት እስከ ምክትል ሚኒስትርነት በነበረው ቆይታ ወያኔያዊ አስተሳሰብ ፍለላንትና እምነት እንዲሰረጽ ለአመታት የሰራ፣ እሱም ብቻም ሳይሆን እሳት የላሱ አፈ ጮሌ ካድሬዎችን አሰልጥኖ ያሰማራ ፣ በመለስ ፊት አውራሪነት ለተፈጸመው ሁሉ አሻራው ያለበት በመሆኑ ዛሬ ለትንሳኤዋ ለተነሱ፣ ለድህነቷ መማሰን ለጀመሩ፣ ኢትዮጵያዊነትን ከልባቸው ላከበሩ፣ ለአንድነታችን እንደገና ማንሰራራት፣ ለታሪካችን ክብርና ለእኛ እኛነት ትልቅነት እንቅልፍ አጥተው መስራት ለጀመሩ ወገኖች ድጋፍ ማበረታታት ነበር ለእነ ኤርምያስ በጎ ተግባር የሚሆነው፡፡ ግን አልሆነም ለምን?

ኤርምያስ አባል በነበረበት ድርጅት ኦህዴድ ተመርጦ ይሁን በበረከት ስምዖን ተስቦ ባይታወቅም ለዛ ከፍተኛ የሥልጣን ደረጃ በደረሰበት ወቅት ለማና አብይ የሚባሉ ሰዎች ኦህዴድ ውስጥ ስለመኖራቸው እንኳን የሚያውቅ ሰው ቢኖር በጣም ጥቂት ይመስለኛል፡፡ ታዲያ እሱ ምኒስቴር ዴኤታ በነበረበት፣ በፌዴራል መንግሥት ደረጃ በሚናንኝበትና በሚታወቅበት ወቅት በድርጅት ውስጥም ሆነ በክልል ደረጃ እውቅና እንኳን ያልነበራቸው ሰዎች ዛሬ ሀገር አድን ሆነው በህዝብ ልብ ውስጥ ተስፋ አሳድረው የፖለቲክ ምህዳሩን ሲቆጣጠሩት፣ የአብዛኛውን ህዝብ ልብ ሰንገው ሲይዙትና አድናቆት ምስጋናና በርቱ የሚለው አዎንታዊ ቃል ሲጎርፍላቸው ኤርምያስን ቅናት ቢጤ ያውም ሰይጣናዊው ሸንቆጥ አድራጋው ይሆን ብዬ ጠረጠርኩ፡፡ ሰይጣናዊ ቅናት ደግሞ መጥፎ ነው በጎ ነገሮችን ሁሉ ማየት የማያስችል ግርዶሽ ይጋርዳል፡፡ ከፍቅር ይልቅ ለጥላቻ፣ከመምከር ይልቅ አቃቂር ለማውጣት፤ከመደገፍ ይልቅ ለመዘለፍ፤ ወዘተ የሚያመዝን ስሜት ይፈጥራል፡፡ ይህም በመሆኑ የቱንም ያህል በጎ ነገር ቢነገርና ቢሰራ አይታይም ወይንም አምኖ ለመቀበል ይቸግራል፣መነጽሩ ቅናት ነውና፡፡ ስለሆነም ወይኔ! ብኖር ኖሮ ከአብይም ከለማም እቀድም ነበር የምትል የቅናት ስሜት ጎብኝታህ ከሆነ በግዜ አውልቀህ ጣላት፡፡አትበጅህም፣አንተ ግንባር ቀደም ተሳታፊ በነበርክበት ሂደት የተፈጠረ ቆሻሻን ለማጽዳትና ቆሻሻው በፈጠረው በሽታ የተጎዱትን ለማከም የሚደረግ ጥረትን አትችልም እንጂ ብትችል ለማምከን የተያያዝከው ጥረት ርጥቡ ሬሳ ደረቅ ያስነሳ ወደሚባለው እንዳያመራ ብታስብበት መልካም ነው፡፡ ስንት ግዜ ትዘምትብናለህ፣ አረ እየተስተዋለ ይሁን፡፡የትናንት በደልን ለነገ መልካም ነገር ሲባል ባይረሳም መተው በዳዩን ለሌላ በደል የሚያደፋፍር መሆን የለበትም፡፡

ሎሬት ጸጋየ ገብረ መድህን በአንድ ግጥሙ እንዲህ ብሎ ነበር፤

የተወጋ በቅቶት ቢኛ የወጋ መች እንቅልፍ አለው፣
የጅምሩን ካልጨረሰው ፤
የተበደለ ቢችልም
ቢሸሽም ቢደበቅም፣
የበደለ ዝም አይልም፡፡

..............

የህሊና ሚዛን ረግቶ ጉዱ ሁሉ ኩልል ሲል፣
የደፈረሰው ሲያጠልል፣
እግዜር ያሳያችሁ ብለህ ፍረዱኝ ዳኙኝ እንዳትል፤
ከነአካቴው ሳይጨርስህ፣
ምን ቢሆን ሰላም አይሰጥህ፡፡

በዘመነ ወያኔ እስር ያልተለየው ጋዜጠኛ እስክንድር ከአሜሪካ ድምጽ ጋር ባዳረገው ውይይት የጽናቱ ምንጭ ፤ የተስፋው መሰረት መጽኃፍ ቅዱስ እንደሆነ ነግሮናል፡፡ እውነት ነው ፈጣሪን ያመነ፤ ቃሉን የተከተለ፤ ጉልበቱ አይዝልም ፤ተስፋው አይጨልምም መንገዱ ደንቃራ ቢበዛበት እንኳን ወድቆ አይቀርም፡፡ ከእውነት ይዛመዳል የፍቅር ሰው ይሆናል፤የበደሉትን ይቅር ይላል፡፡ ብዙዎቻችን ዘንድ ግን እምነት በመጥፋቱ ፈሪሀ እግዚአብሄር በመራቁ ነው፤ሀሜት፣ አሉባልታ ፣ ጥላቻ መዝራት በጎ በሚሰሩ ሰዎች ላይ አቃቂር ማውጣት የእለት ተግባራችን አንድ አካል የሆነው፡፡ አንድዬ የማሪያም ልጅ በኪነ ጥበቡ ወደ ራሱ ይመልሰን፡፡

ለዚህ ጽሁፍ ምክንያት የሆነኝ ኤርሚያስ የእምነት ደረጃውን ባላውቅም በቅዱስ መጽኃፍ ጥቅስ የጀመርኩትን ጽሁፍ በዚሁ መንገድ መቋጨትን ወደድሁ፡፡ የያዕቆብ መልእክት ምዕራፍ 3 ከቁጥር 16 – 18 እንዲህ ይላል፡ ፡ *"ቅንአትና አድመኝነት ባለበት ስፍራ በዚያ ሁከትና ክፉ ሥራ ሁሉ አሉና ላይኛይቱ ጥበብ ግን በመጀመሪያ ንጽህት ናት፤በኋላም ታራቂ ገር እሺ ባይ ምህረትና በጎ ፍሬ የሞላባት ጥርጣሬና ግብዝነት የሌለባት ናት፡፡ የጽድቅም ፍሬ ሰላምን ለሚደርጉ ሰዎች በሰላም ይዘራል፡፡ "*